የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ
TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: czanareg@hotmail.com

# በወገን ሰቆቃና በሉዓላዊ ግዛቶቻችን ችሮታ የሥልጣን ዕድሜ ማራዘም ከቶም አይቻልም።

የኢህአዴግ መሪዎች የሥልጣን ዕድሜቸውን ለማስጠበቅ ያስችላል ብለው የገመቱትን ለማሳካት የማይፈፅሙት ግድያ፣ የማይፈጥሩት ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያናቁር ተንኰል፣ የማይነዙት ውሸት፣ የማይፈጥሩት በሬ ወለደ ታሪክ እንደሌለና እንደማይኖር ለመገንዘብ ከቻልን ዓመታት አስቆጥረናል። በተግባር ተቃራኒውን እየፈጸሙ በአፍና በጽሑፍ መግለጫዎች  ለጆሮ የሚጥም መና ሊያግቱን ከሞከሩ ሰንበትበት ብለዋል። የተናገሩትንና የጻፉትን ስንመለከት ተግባርና ምናብ ለየቅል መሆናቸውን በሚገባ እንገነዘባለን።

የኢህአዴግ መሪዎች ስለ ሉዓላዊነት መከበር፣ ስለ ድህነት ቅነሳ፣ ስለ ብሔር ብሔረ-ሰቦች እኩልነት፣ ስለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ፣....... ወዘተ. ለሰሚ ጆሮ በሚጥም መልኩ እያቀረቡ በተግባር ሲተረጉሙት ግን ጭራሽ በተቃራኒው እንደሚጓዙ ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝቦች መንገር የሚገባን ዜና ነው ብለን አናምንም። ስለ ድህነት ቅነሳ ሲነግሩን ኢኮኖሚው በየዓመቱ በሚያስገርም ሁኔታ እያደገ ነው ይላሉ። በተግበር ሲታይ ግን ህዝባችን ከዓመት ዓመት በከፋ ድህነት ሲሰቃይ እናያለን። የብሔር ብሔረ-ሰቦች እኩልነት ተረጋግጧል ሲሉን አድምጠን በተግባር ሲታይ ግን ብሔር ብሔረ-ሰቦች በመብት እጦት ከመሰቃየት አልፈው በእርስ በርስ ግጭት ሲተላለቁ እንታዘባለን። በመሆኑም የብሔር ብሔረ-ሰቦች መብት የኢህአዴግ መሪዎች የከፋፍለህ ግዛ እኩይ ተግባር ማስፈጸምያ ከመሆን ያለፈ እንዳልሆነ በተግባር አይተነዋል። ስለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጣፋጭ ቃላት ሲነገር ብንሰማም የኢህአዴግ መሪዎች ዴሞክራሲ የነሱን ፍላጎት እስካሳካ ድረስ ብቻ እንጂ የዜጎችን መብት ለማስከበር እንዳልሆነ በግዙፍ ማስረጃ በማስደገፍ ለመተንተን እንደሚቻል ህዝባችን ያውቀዋል።

ታዲያ ዛሬ የኢህአዴግ መሪዎች ሉዓላዊ ግዛቶቻችንን ለሱዳን አሳልፈን አልሰጠንም ቢሉ ማመን ይቻላልን? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ብዙ ምርምር የሚያስፈልገው አይደለም። አንድ አገርን የሚያስተዳድር ኃይል በአገሪቱ ውስጥ ለሚያከናውናቸው ሁለመናዊ ሥራዎች መሳካት በመጀመርያ ደረጃ በሚያስተዳድረው ህዝብ መታመን ይኖርበታል። በዜጎች ለመታመን ደግሞ ከቅጥፈትና ማታለል ራሱን ነፃ ማውጣት ይጠበቅበታል። የሚያከናውናቸው አገራዊ ሥራዎች ለህዝብ በግልጽና በሓቅ ማቅረብ አለበት። ህዝብ የአገሩ ጉዳይ ቀጥተኛ ባለቤት መሆኑን ተገንዝቦ ማነኛውም አገርን የሚመለከት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት እንዲወያይና እንዲወስን ይገፋፋል፣ ሁኔታዎችምን ያመቻቻል፣ የህዝቡን ውሳኔንም ያከብራል ያስፈጽማልም።

የኢህአዴግ አመራር ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ህዝቦች ህልውና ላይ እየፈጸመው ያለው ደባ ግን ከላይ የጠቀስነውን ህዝባዊና ሀገራዊ ግዴታ በቀጥታ የሚፃረር ሆኖ ይገኛል። ዛሬ የአህአዴግ አመራር የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶች  ለሥልጣን ማስጠበቅያ እንዲያገለግለው በማን አለብኝነት ለሱዳን ማስረከቡ የሱዳን መንግሥት ባለሥልጣናትና

የሱዳን መገናኛ ብዙኃን በሰፊው እያቀረቡትና እየዘገቡት የሚገኙ ቢሆንም ኢህአዴግ እየተደራደርኩ ነው እንጂ የኢትዮጵያ ግዛቶችን አሳልፌ አልሰጠሁም እያለ በለመደው ቅጥፈት ሊያወናብደን እየሞከረ ነው። በመሬት ላይ ያለው ሁኔታ የሚመሰክረው ግን ትክክለኛው የምናውቀው የተለመደው የኢህአዴግ መሪዎች ክህደት ነው። በሱዳን ድንበር ነዋሪ ህዝባችን ላይ የደረሰውና በመድረስ ላይ የሚገኘው ግፍና ሰቆቃን አስመልክቶ የኢህአዴግ አመራር ለኢትዮጵያ ህዝብ ለመግለጽ የሚያስችል የሞራል ብቃት አላገኘም። ይባስ ብሎ የኢህአዴግ አመራር እንደለመደው ምንም ችግር የለም፣ “ፀረ-ህዝብ” ኃይሎች የሚያቀርቡት ፕሮፓጋንዳ ነው በማለት ህዝብን ለማደናገር በመሯሯጥ ላይ ናቸው።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ህዝቦች ያለፉትን ክህደቶች በሚገባ ዘግበው የያዙት በመሆኑ እንዲህ በቀላሉ የሚታለሉ አለመሆናቸው ይህ አገዛዝ አላወቀም። የኢትዮጵያ ህዝቦች የኢህአዴግ መሪዎች የክህደት ባህሪያትን ጠንቅቀው ተረድቷል። “መጀመርያ ጊዜ ሲያታልለኝ ሞኙ እኔ አይደለሁም፣ ሁለተኛ ደግሞ ቢያታልለኝ ግን እኔ ሞኝ ነኝ” የሚለውን የፈረንጆች አባባል ለዚህ ሁኔታ እጅጉን ይሰማማል። የኢትዮጵያ ህዝቦችን አንድ ጊዜ ለማታለል መሞከር ይቻላል። ሁሌ ለማታለል መሞከር ግን የህዝብን ብልህነትና ክብር መዳፈር መሆኑን በሚገባ ይገነዘባሉ። እዚህ ላይ ለግንዛቤ ያህል ወደ ኋላ መለስ ብለን አንድ ነገር ማውሳት ጠቃሚ ይመስለናል።

ከዚህ በፊት የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ጦርነት ተካሂዶ የኢትዮጵያ ህዝቦች በከፍተኛ መስዋእትነት ያስከበሩትን ሉዓላዊነት አቶ መለስ ዜናዊ አልጀርስ ላይ እንዴት አስረክቦ እንደተመለሰና ለኢትዮጵያ ህዝቦች የሚጠቅም ተግባር ፍጻሜ ተመለስኩ የሚል “የምሥራች” ማስነገሩ ይታወሳል። ሁኔታው ፍርጥርጥ ብሎ እስኪወጣ ድረስ የተወሰነን ወገን አደናግሮ እንደነበረም ይታወቃል። እ.ኤ.አ ሚያዝያ 13 ቀን 2002 ዓ.ም ሄግ ላይ የድንበር ውሳኔ ብይን ሲያገኝ ምንም ነገር እንዳላጣን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ነገር እንዳሸነፍን በማስመሰል “በጦር ሜዳ ያስመዘገብነው ድል በፍርድቤት ደገምነው፤ ሉዓላዊ መሬቶቻችን ለኢትዮጵያ ተበይኗል” በማለት ዓይናቸውን በጨው አጥበው ሊያታልሉን መከጀላቸው እንዲህ በቀላሉ ተዘናግተን የምናልፈው አይደለም። ያኔ የኤርትራው ሻዓቢያ “የሄግ ፍርድቤት የድንበር ሙግቴ ትክክለኛነት በሰጠው ብይን አረጋግጦልኛል” ሲል የኢህአዴግ መሪዎች፣ ሻዓቢያ ውሸቱን ነው፣ ሉዓላዊ መሬቶቻችን ብቻ ሳይሆን የነሱንም መሬት ለኛ ተወስኖልናል እያለ ነበር ሊያታልለን የከጀለው። ዛሬም የሱዳን መንግሥት ኢህአዴግ አመራር የጠየቅኳቸውን ግዛቶቼን ሰጥቶኛል ሲል፣ የኢህአዴግ አምባገነናዊ አመራር ግን ለሱዳን መሬት አልሰጠሁም ገና በመደራደር ላይ ነኝ ይለናል። የሱዳን መንግሥት ባለሥልጣናት መግለጫ ላይ የሰጠው ማስተባበያ ግን የለም። እንዲሁ እኛን ለማባባል የቢሮ ስርኩላር ይመስል እኔ መሬት አልሰጠሁም ነው የሚለን ያለው። ሃቁ ይህ ነው። ኢህአዴግ የጠየቅኳቸው ግዛቶቼን አስረክቦናል ሲሉ የሱዳን ባለሥልጣናት በሬዲዮና በጋዜጣ ይፋ መግለጫ ሰጥተውበታል። የሱዳን ባለሥልጣናት ይህንን መግለጫ በውሸት የሚሰጡት ምን ሊያገኙበት ይሆን? የሚለው ጥያቄ ባገባቡ መልስ ማግኘት ይኖርበታል። ሱዳኖች ትላንትናም ሆነ ከትላንት ወዲያ እንዲህ ዓይነት መግለጫ ሲሰጡ አልተሰማም። ዛሬ ዋሽተው ይህንን መግለጫ ሊሰጡ የሚያስገድዳቸው አዲስ የተፈጠረ ሁኔታ የለም። በመሆኑም ይህ የሱዳን ባለሥልጣኖች መግለጫዎች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ መሬቶች ለሱዳን መቸራቸውን ያረጋግጥልናል። ከላይ እንደገለጽነው ያለፈውን ህዝብን እየደጋገሙ ለማታለል የመሞከር ባሕሪያቸውን ዛሬ ላይ ደርሰው አርመውታል ሊባል ከቶም አይቻልም። ይህ አገዛዝ ህዝብን ሳያታልል ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችለው ነገር የለውም። ህዝብ እንደነቃባቸው ጠንቅቀው ቢያውቁም ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው የህዝብን የእይታ አቅጣጫ ለማስቁር ይረዳል

ብለው የሚያስቡትን ከመሞከር ለመቆጠብ አይችሉም። በኢትዮጵያ ህዝቦች እንደተተፉ ጠንቅቆ ያውቃልና።

በመሆኑም ለኢትዮጵያ ህዝቦች የሚከተሉትን ጥሪዎች ለማስተላለፍ እንወዳለን።

1. የኢህአዴግ መሪዎች የክህደትና የማታለል ተፈጥሮ በተደጋጋሚ የታየና የምናውቀው ነው። ስለሆነም የአገር ባለአደራ የኢትዮጵያ ህዝቦች ብቻ እንደመሆናቸውና የሚታመኑ የአገር መሪዎች እንደሌሉን ተገንዝበው ለሉዓላዊነታቸው መከበር ዛሬም እንደትላንቱ ዘብ እንዲቆሙና፣ የኢህአዴግ የክህደት ተፈጥሮ ተደጋግሞ የተመሰከረ በመሆኑ ካለፈው ልምድና በየዕለቱ የሚታየውን የማጭበርበር ተግባር ግንዛቤ ውስጥ እንዲያስገቡ።

2. ዛሬ የኢህአዴግ መሪዎች ለሱዳን መንግሥት ተቃዋሚ እንዲከላከልላቸው ለውለታ የቸሩት መሬት በአባቶቻችንና በእናቶቻችን ደምና አጥንት ተከብሮ የኖረ ሉዓላዊ የኢትዮጵያ ግዛት በመሆኑ ሉዓላዊ ግዛቶቻችን እንዲከበሩ ከኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጎን በመሰለፍ ትግላቸውን እንዲያጠናክሩ።

3. የሱዳን መንግሥት በኢህአዴግ መሪዎች ከተቸረለት ሉዓላዊ ግዛታችን በጉልበት ያፈናቀላቸው ዜጎቻችን በአገራቸው ወደ ቀያቸው ተመልሰው ዋስትና ያለው ሰላማዊ ሕይወት እንዲመሩ ማስቻል የእያንዳዳችን ግዴታ መሆኑን በመገንዘብ ከነዚህ ወገኖች ጎን በመቆም ተባብረን ከሰቆቃ እንዲወጡ የተቻለውን ሁሉ እንድናደርግ።

4. ድርጅታችን ት.ዴ.ት ከኢህአዴግ መሪዎች የሚጠበቅ የአገርና የወገን ፍቅር አለ ብሎ አያምንም። በመሆኑም ለኢህአዴግ መሪዎች የሚያቀርበው ጥሪ ፈጽሞ አይኖርም። ይህ ኃይል ሥልጣን ላይ እስከቀጠለ ድረስ ነገም ለሶማሊያ፣ ለጅቡቲና ለኬኒያ የሚሰጡ ሉዓላዊ ግዛቶቻችን እንደሚኖሩ አንጠራጠርም። በመሆኑም ከተደጋጋሚ ድፍረትና ክህደት ለመዳን የሚያስችለን ወሳኙ መንገድ ይህንን ኃይል ከሥልጣን አስወግዶ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመተካት ብቻ መሆኑን በማመን ክንድን አስተባብሮ በመታገል ለትውልዶች የሚተላለፍ አገር እንዲኖረን ለመሥራት ታጥቆ እንዲነሳ።

5. ዛሬ ከኢህአዴግ ጀምሮ የፖለቲካ ስብእና አለን የሚሉ ግለሰቦችን ጭምር አንዳንድ ወገኖች ህዝብን እንደ ህዝብ በመወረፍ ላይ ይገኛሉ። ት.ዴ.ት ይህንን ዓይነት አስነዋሪ ተግባር ይኮንናል ይታገላልም። ማንም ህዝብ የራሱ የሆነ ክብር እንዳለው አጥብቀን ስለምናምን ህዝብን እንደ ህዝብ ለማቃለል የሚሞክሩ ኃይሎች የተሳሳተ መንገድ እንደያዙ እንውቃለን። ይህ መንገድ ደግሞ አባቶቻችንና እናቶቻችን በመስዋእትነት ያቆዩልንን አገር ከማፍረስ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝቦች እነዚህ አፍራሽ መልእክተኞች ከአጸያፊ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ ግልጽ መልእክት እንዲያስተላልፉ፣

6. የኢትዮጵያ አገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊያን ኃይሎች ይህ የህዝብን ሥልጣን በጉልበት የነጠቀው ጨካኝ ኃይል ማስወገድ ቢፈልጉም የእስካሁኑ የተናጠል ትግላቸው የሚፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ አልቻሉም ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም በተናጠል የሚደረገው ትግል ወደ ውጤት አያደርሰንም የሚል ስጋት አለን። ይህ ጨካኝ ኃይል ካልተወገደ ደግሞ ብሔራዊ ጥቅማችን ላይ ያነጣጠረው አደጋን

ማስቀም አንችልም። ስለሆነም ትግላቸውን አስተባብረው ለዘላቂ መፍትሔ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁና እንዲተባበሩ ዛሬም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ደም ለዘላለም ተከብራ ትኖራለች!!!**
**ሉዓላዊ ግዛቶቻችን በከሃዲዎች ችሮታ አይደፈሩም!!!**
**አንድነታችን በህዝባዊ ትግል ተጠናክሮ በድል ይገባደዳል!!!**

**ት.ዴ.ት**

**ግንቦት 2000 ዓ.ም**